## ዛፎቹ ምን ያደርጋሉ - המשך פעילויות בעקבות הסיפור

በ: ዓይን ሂሌል
ምሳሌዎች: ዳቪድ ፖሎንስኪ
הוֹצָאָה: ספרית פועלים
የእድሜ ክልል: ቅድመ ትምህርት ቤት




קְרִיאָה

**ለቤተሰባዊ ንባብ የሚሆን ጠቃሚ ምክር**

በሥዕል የተደገፈ መጽሐፍ የሚሆን የተቀናበረ ግጥም አንባቢዎች በተለየ መንገድ እንዲለማመዱት፣ እንዲረዱት ወይም እንዲያውቁት ዕድል ይሰጣል። ስለዚህ ይህንን ዓይነት መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ስታነቡ “መጽሐፉን ለመዘመር” መሞከር የለብዎትም ነገር ግን ለሁሉም ነገር እንደ ታሪክ ሆኖ ያንብቡት።

ዓይን ሂሌል (1926-1990) ድንቅ የህፃናት መጽሃፍ ደራሲና ገጣሚ ተወልዶ ያደገው በኪቡዝ ሚሽማር ሀዔሜክ ነው። በሙያው የመዋእለ ህጻናት አርክቴክት ነበር። ነገር ግን ለትንንሽና ትልልቆች መዝሙሮችን መጻፍ ከሁሉም በላይ ይወድ ነበር። በእሥራኤል ውስጥ ካሉት አንጋፋ ሠዐሊዎች አንዱ የሆነው ዳቪድ ፖሎንስኪ ለፊልሞች አኒሜሽን ፈጥሯል፣ በብዙ ኤግዚቢሽኖች ላይ አሳይቷል፣ ሽልማቶችንና ዓለም አቀፍ እውቅና አግኝቷል።

שִׂיחָה

**ጊዜው እንዲሁ ያልፋል**

ጥያቄዎች ውይይትንና ሀሳብን ያበረታታሉ። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምሳሌዎች መመልከትና መጠየቅ ይችላሉ፡-

ልጁ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ምን ያደርጋል? የመጽሐፉን መጀመሪያ እንዴት ይመለከታል? መጨረሻውንስ? በምስሎች ተመስጦ ካለፉት ጊዜያት ፎቶዎችዎን አንድ ላይ ማየት ይችላሉ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንዴት እንዳደጉ ይመልከቱና ጥያቄዎችን ይጠይቁ – የአንድ ዓመት ልጅ ሳለሁ ምን አደረግሁ? አሁንስ ምን አደርጋለሁ? ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምን ?አገኘሁ እና ተማርኩ

חֵקֶר

**?ምን እናድርግ**

የልብስ ማጠቢያ ማሽን ምን ያደርጋል? ጣሪያውስ ምን ያደርጋል? ታሪኩን ተከትለው በቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ”?በመራመድ በዙሪያዎ ስላዩዋቸው ነገሮች መጠየቅ ይችላሉ “ምን እያደረጉ ነው

יְצִירָה

**ዓለምን ማግኘት**

መጽሐፉ የተለያዩና አዝናኝ መልሶች ያላቸው ብዙ ጥያቄዎች አሉት። መጽሐፉ በጥልቀት እንዲያጤኑና አብረው እንዲመረምሩ ይጋብዝዎታል። ልጆችዎን መጠየቅ ይችላሉ – ዛፎቹ ሌላ ምን ያደርጋሉ? ደመናዎችስ ሌላ ምን ያደርጋሉ? እንዲሁም የራስዎን የጥያቄና መልስ መጽሐፍ በመያዝ በጋራ መስራት ይችላሉ። ይጻፏቸውና ይሳሉዋቸው እና ሌላ ጥያቄ በተነሳ ቁጥር ወደ ታሪኩ ጨምረው መልሱን መፈለግ ይችላሉ።

שְׁמַע

**QR ኮድ**

በጣም የታወቀውና የተወደደው የዓይን ሂሌል መዝሙር የተቀናበረው በኑኃሚን ሼሜር ሲሆን ቀድሞውኑ የእስራኤል

ክላሲክ ሊሆን ችሏል። ለማዳመጥ ኮዱን ስካን ያድርጉ።

הַשְׁרָאָה

**ፒንተረስት**

ተጨማሪ ስራዎች፣ መዝሙሮችና እንቅስቃሴዎች በፒጃማ ቤተ መጻህፍት ፒንተረስት ላይ ይገኛሉ።

www.pjisrael.org עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה